DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS







# የልዩ ትምህርት (Special Education) ፕሮግራሞች እና የመገኛ ምንጮች (Resources) መመሪያ፤ ለቤተሰቦች

# የትምህርት ዓመት 2021-2022

## ማውጫዎች


የልዩ ትምህርት (Special Education) ሂደት ላይ፣ የአንዳፍታ ምልከታ ....3
የልዩ ትምህርት (Special Education) ሂደት ላይ፣ የአንዳፍታ ምልከታ ....4
ልጄ፤ ልዩ የትምህርት (special education) አገልግሎቶች ያስፈልገዋል ብዬ ካመንኩኝ፣ ማንን ማነጋገር አለብኝ?....5
ቅድመ-ደረጃዎች (Early Stages):....6
በብቁነት ሂደቱ-ወቅት ልጠብቀው የሚገባው ነገር ምንድነው?....7
በIEP ውስጥ፣ ምንን መመልከት ያስፈልጋል? ....9
ስለልጅዎ IEP፣ ሊኖሩ የሚችሉ ጥያቄዎች ....11
ልጄ እድገት እያመጣ መሆኑን እንዴት ማወቅ እችላለሁ? ....13
ልዩ ትምህርት (special education) አገልግሎቶች የት ይሠጣሉ? ....14
ልዩ ትምህርት (special education) አገልግሎቶች የት ይሠጣሉ? ....15
ለልዩ ትምህርት የተዘጋጀ (Self-Contained) ፕሮግራም ዓይነቶች ....16
የአገልግሎት ቦታዎች (Location of Services (LOS):....17
የሽግግር ፕሮግራሞች (Transition Programs) ....18
አጋዥ የሆኑ ቴክኖሎጂ (Assistive Technology) ....19
ተዛማጅ የሆኑ አገልግሎቶች (Related Services) ....20
የተመረጠ 504 ፕሮግራም ....21

# የልዩ ትምህርት (Special Education) ሂደት ላይ፣ የአንዳፍታ ምልከታ

ልጁ በዚህ አጠቃላይ ሂደት የጣልቃ ገብነት ምላሽ ወቅት፣ (response to intervention - RTI) ማግኘት ይችል ይሆናል።

ልጅዎ አንዳች የሆነ እክል ሊኖርበት ይችል ይሆናለ ተብሎ ተጠርጥሯል።

እርስዎ ወይም ከልጅዎ ጋር ቅርብ የሆነ ሰው፣ ወደ ልዩ ትምህርት (special education) አገልግሎቱ፣ ሊመራ (referral) ችሏል።

የIEP ቡድኑ መመራሩትን (referral) ተቀብሎ፣ በአሁኑ ወቅት ያለውን የተማሪ የመረጃ ስብስብ (data)ን ይመለከታል፣ እና ልጁ ተጨማሪ ግምገማዎች ያስፈልጉት አያስፈልጉት ይወስናል።

*ይህ ሂደት በሚካሄድበት ጊዜ ሁሉ፣ መመራቱ (referral) ላይ ምልከታ ማድረግ ትችላላችሁ።*

30 ቀናት

የIEP ቡድን በዚህ ሰዓት ግምገማ እንደማያስፈልግ ይወስን እና ከማብራሪያ ጋር በጽሑፍ

ያስታውቅዎታል።

ልጅዎ ለልዩ ትምህርት (special education) አገልግሎቶቹ ብቁነት አይኖረውም።

ትምህርት ቤቱ ድጋፍ መስጠቱን ይቀጥላል፤ እና የእድገቱን እንቅስቃሴዎችን ይከታተላል።

የIEP ቡድን ግምገማ እንደሚያስፈልግ ይወስን እና በጽሁፍ ያስታውቅዎታል።

የIEP ቡድኑ ለግምገማ እና ግምገማውን ለማካሄድ የእርስዎን ስምምነት ይጠይቃል። ግምገማው በተለይ ለልጅዎ እንዲያመች ተደርጎ የሚዘጋጅ ሲሆን፣ ምልከታዎችን፣ ቃለ-መጠይቆችን፣ የትምህርት ውጤት ማሳያ ካርድን የማጣራት ምርመራን፣ እና/ወይም ግምገማን ሊያካትት ይችላል።

60 ቀናት

ልጅዎን ብቁ የሚያደርገው አንዳች እክል ስላለበት፤ የልዩ ትምህርት (special education) አገልግሎቶች ያስፈልጉታል።

30 ቀናት

ለልጅዎ የሚያስፈልገው የአገልግሎቶች ደንብ ማስጀመሪያ እንዲዘጋጅለት እና የIEP ቡድኑ፣ የሚያስፈልገውን IEP እንዲቀርጽ፣ ተስማምተዋል።

የትምህርት ቤት ሠራተኛው፣ IEPውን ሥራ ላይ ያውላል።

# የልዩ ትምህርት (Special Education) ሂደት ላይ፣ የአንዳፍታ ምልከታ

የልዩ ትምህርት (special education) ሂደት፣ የሚጀምረው ከልጁ ጋር ትውውቅ ያለው ግለሰብ፣ የልዩ ትምህርት (special education) አገልግሎቶች እንዲሰጠው መምራቱን (referral) ሲያስገባ፤ ወይም በቃል ጥያቄውን ሲያቀርብ ነው። መመራቱን (referral) ሊያስገቡ የሚችሉት እነማን እንደሆኑ በምሳሌነት ለማቅረብ፤ ወላጆች/አሳዳጊዎች፣ አስተማሪዎች፣ የሥነ ልቦና ባለሞያዎች፣ ሌላ የትምህርት ቤት የሥራተኛ አባሎች፣ የህፃናት ጥበቃ ማዕከል (day care center) ሠራተኞች፣ ሐኪሞችን ያካትታል።

**የIEP (የግላዊ የትምህርት ፕሮግራም)** ቡድን፣ የመመራቱ (referral) እና በዚህ ቀደም የተሰበሰቡ የመረጃ ስብስቦችን (data)፣ ማንኛውም ከዚህ በፊት የተደረጉ ግምገማዎችን ጨምሮ፤ ለመወያየት ይሰበሰባሉ። የIEP ቡድን፤ ወላጆችን/አሳዳጊዎችን፣ ልጁን (ተገቢ ነው ተብሎ ከታመነ)፣ የልዩ ትምህርት (special education) አስተማሪዎችን፣ የአጠቃላይ ትምህርት አስተማሪዎችን፣ ተዛማጅ የሆኑ አገልግሎት ሰጪዎችን፣ እና/ወይም ሌሎች ቁልፍ የሆኑ የትምህርት ቤት ሠራተኞችን ያካትታል።

በቂ-የሆነ የመረጃ ስብስብ (data) ካለ፤ የIEP ቡድኑ፣ ልጁ ለልዩ ትምህርት (special education) አገልግሎቶች ብቁ መሆኑን የሚወስን፣ ወይም ተጨማሪ ግምገማዎች እንዲደረጉ እና የብቁነት መወሰኛ ስብሰባው እንደገና እንዲደረግ ሃሳብ-ሊያቀርቡ ይችላሉ። ልጁ አንዳች የሆነ እክል ያለበት በመሆኑ፣ ለልዩ ትምህርት (special education) አገልግሎቶች ብቁ ሆኖ ከተገኘ፤ የIEP ቡድኑ የእርምጃ ዕቅዱ ላይ ተወያይቶ እና የIEP ዕቅዱን ያዘጋጃል።


IEPው፣ የልጁን ዓመታዊ የትምህርት ግቦችን የሚነድፍ ሠነድ ሲሆን፣ የትምህርት አሰጣጥ እና ተዛማጅ አገልግሎቶችን ጨምሮ፣ እነዚያን ግቦች ለመምታት የሚያስፈልጉ ናቸው። እነዚህ አገልግሎቶች ሊሰጡባቸው የሚችሉበትን ተገቢ-የሆነውን አቀማመጥ፤ IEPው ይጠቁማል።

የልጅዎ አሳዳጊ እንደመሆንዎ መጠን፣ በIEP ቡድኑ ውስጥ በጣም የሚያስፈልጉን አባል ነዎት። በ2014 በወጣው የልዩ ትምህርት የተማሪ መብቶች ድንጋጌ (Special Education Student Rights Act of 2014) በሚጠይቀው መሠረት፣ በIEP ወይም የብቁነት መወሰኛ ስብሰባ ላይ ውይይት የሚደረግባቸውን ማንኛውንም አግባብ-ያላቸውን ጠቃሚ ሰነዶችን፣ ከስብሰባው 5 የሥራ ቀናት በፊት ቀደም ብሎ የልጅዎ ትምህርት ቤት እንዲልክልዎ ይጠይቀዋል። ይህም መረጃዎቹን ለመመርመር እና ለስብሰባው እንዲዘጋጁ በቂ ጊዜ ማግኘትዎን ለማረጋገጥ ነው። በዚሁበተጠቀሰው ህግ ስር፣ ስብሰባው ከተካሄደ በኋላ ባሉት 5 የሥራ ቀናት ውስጥ፣ የIEPውን ቅጂ እንደሚላክልዎ ሊጠብቁ-ይችላሉ።

እያንዳንዱ ተማሪ በሚማርበት ወይም በክልል አጎራባች ትምህርት ቤቱ ውስጥ፣ የልዩ ትምህርት (special education) አገልግሎትን እንዲያገኝ ለማድረግ፣ DCPS አስፈላጊውን ጥረት ሁሉ ያደርጋል። ይህ የማይቻል ሲሆን፣ DCPS ለተማሪው መኖሪያ-ቤት በጣም በቅርበት ወደሚገኝ ወደ አዲስ አገልግሎት መስጫ ክልል እና IEPውን በታማኝነት ለማስፈጸም ወደሚቻልበት አገልግሎት መስጫ ይመድበዋል። በ2014 የወጣው የልዩ ትምህርት የተማሪ መብቶች ድንጋጌ (Special Education Student Rights Act of 2014)፣ ወላጆች ወይም በእነሱ የተወከሉ ሰዎች፣ በወቅቱ ያለውን ወይም ወደፊት የታሰበውን የልጃቸውን የክፍል ውስጥ ጉብኝት እንዲያደርጉ ይፈቅድላቸዋል። ልጅዎን የሚከታተል ሌላ ተወካይ መመደብ ሲፈልጉ፣ ትምህርት ቤቱ ለዚሁ ተግባር ሲባል የተዘጋጀ የታዛቢ ተወካይ ቅጽ (Observation Designee Form) ይሰጥዎታል።



# ልጄ፤ ልዩ የትምህርት (special education) አገልግሎቶች ያስፈልገዋል ብዬ ካመንኩኝ፣ ማንን ማነጋገር አለብኝ?




በDCPS ውስጥ፣ ወደ ልዩ ትምህርት (special education) አገልግሎቶች የሚደረጉ መመራቶች (referrals) ወደሚከተሉት ቡድኖች ተደርገዋል:

- **ቅድመ-ደረጃዎች (Early Stages)ን በ(referral@earlystagesdc.org) ወይም (202) 698-8037)** - መምራቶችን (referrals) የሚቆጣጠረው፣ ዕድሜያቸው ከ3 እስከ 5 ለሆኑ በዲሲ የግል ወይም የሃይማኖት ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚማሩ ልጆች፤ እንዲሁም እስካሁን በትምህርት ቤት ያልተመዘገቡ ልጆችንም ጭምሮ።

- **የDCPS የክልል አጎራባች ትምህርት ቤቶች (profiles.dcps.dc.gov - ለትምህርት ቤት የመገኛ-አድራሻ መረጃዎች)** - ዕድሜያቸው ከ3 እስከ 21 የሆኑ ተማሪዎች በDCPS ውስጥ ተመዝግበው፤ ከሚማሩበት ትምህርት ቤት፣ የተመሩ (referred የተደረጉ)።

- **ማዕከላዊ የሆነ የIEP እርዳታ (dcps.childfind@k12.dc.gov ወይም (202) 442-5475)** - ማዕከላዊ የሆነ የIEP እርዳታ ክፍል፤ ዕድሜያቸው 5 ዓመት ከ10 ወራት የሆኑ ልጆች እስከ 21 ዓመት ዕድሜ የተመሩትን ቁጥጥር የሚያደርግ ሲሆን፤ በወላጅ፣ በግል እና በሃይማኖት ትምህርት ቤት ውስጥ ለተመደቡ እና የገንዘብ ድጋፍ ለሚደረግላቸው፤ ከሚከተሉት በአንዱ ስር የተመደቡ:
  - ቤተሰቡ በዲሲ ውስጥ መኖሪያቸው ሆነም አልሆነ፤ በዲሲ ውስጥ የግል ወይም የሃይማኖት ትምህርት ቤት ውስጥ የሚማሩ፤
  - ቤተሰቡ በዲሲ ውስጥ መኖሪያቸው የሆነ እና፤ በሌላ ስቴት ውስጥ በግል ወይም የሃይማኖት ትምህርት ቤት ውስጥ የሚማሩ፤ ወይም
  - በዲሲ ውስጥ፣ በመኖሪያ ቤታቸው ውስጥ (home schooled) የሚማሩ።

ማዕከላዊ የሆነው የIEP ክፍል፣ ተማሪዎችን ለልዩ ትምህርት (special education) አገልግሎቶች የግምገማ ሂደት በሚያካሂድ ጊዜ፣ የሚከተሉትን መረጃዎች እንዲቀርቡ ይጠይቃል:

- የመመራት (Referral) ቅጽ
- ዓለም አቀፍ የጤና (Universal Health) ቅጽ
- በዲሲ ውስጥ፣ በግል ወይም በሃይማኖት ትምህርት ቤት ውስጥ የተመዘገቡ ለመሆኑ ማረጋገጫ (አብዛኛውን ጊዜ ከትምህርት ቤቱ የተፃፈ ደብዳቤ)
- የዲሲ ነዋሪነት ማረጋገጫ (ለዲሲ ነዋሪዎች ብቻ፣ ሌሎቹ ሰነዶች ገቢ ከሆኑ በኋላ የሚሞላ)
- ተጨማሪ፣ ያስፈልጋሉ ተብሎ የተጠቀሱ መረጃዎች:
  - በትምህርት ገበታ ላይ መገኘትና አለመገኘት (Attendance) መዝገቦች
  - ሪፖርት ካርዶች
  - መሠረታዊ የሆኑ የፈተና ውጤቶች (Standardized test scores)
  - የሥራ ናሙናዎች (Work samples)
  - ከዚህ ቀደም የነበሩ ግምገማዎች (ካለ)

# ቅድመ-ደረጃዎች (Early Stages):

የመገኛ-አድራሻ መረጃ: referral@earlystagesdc.org ወይም info@earlystagesdc.org

እንደ IDEA አሠራር መሠረት፣ የትምህርት ቤት ዲስትሪክት አንዳች የሆነ እክል ይኖርባቸው ይሆናል ተብለው የሚገመቱ ከ3- እስከ 5-ዓመት የሆናቸውን ልጆች ፈልጎ መለየት፣ የት እንደሚገኙ ማወቅ እና መገምገም አለበት። ቅድመ ደረጃዎች (Early Stages)፣ በግል እና በሃይማኖታዊ ትምህርት ቤቶች በሚማሩ፣ በሕጻናት መንከባከቢያ ማዕከላት፣ እና ትምህርት ቤት ገና ካልተመዘገቡ ልጆች ጋር ይሠራል። በተጨማሪም፣ ቅድመ-ደረጃዎች (Early Stages)፣ ልጆች ሶስት ዓመት ዕድሜ ከመሆናቸው በፊት፣ የቅድመ ጣልቃ-ገብነት አገልግሎቶች እንዲሰጣቸው ሂደቱ፤ ለልዩ ትምህርት (special education) አገልግሎቶቹ ብቁ የሆኑን፣ በትምህርት ቤት ውስጥ - በሦስት-ዓመት ዕድሜያቸው ወይም ከዚያ በኋላ፣ ማግኘት-አለማግኘታቸውን የሚወስነውን፣ የክፍል (Part) C ሽግግር (Transition)ን ላይ ቁጥጥር ያደርጋል።

ቅድመ ደረጃዎች (Early Stages)፣ ሁለት የግምገማ ቦታዎች አሉት:


- ዋከር-ጆንስ (Walker-Jones) የትምህርት ካምፓስ፤ 1125 New Jersey Avenue, NW
- የቅጥር-አገልግሎቶች (Employment Services) መምሪያ፣ 4058 Minnesota Avenue, NE

## ዋና ተግባራት (Main Activities)

ቅድመ ደረጃዎች (Early Stages) የእድገት መዳበር ምርመራዎችን ይሰጣል፣ ወደ ሌላ መምራትን (referrals) መቆጣጠር፣ ምዘናዎችን ማከናወን፣ የብቁነት ስብሰባዎችን ያካሂዳል፣ IEPዎችን ይነድፋል፣ ብቁ የሆኑ ልጆች አገልግሎቶቻቸውን እንዲያገኙ ቦታዎችን ፈልጎ ያመቻቻል። እያንዳንዱ ወደ ሙሉ ግምገማ የተመራ ተማሪ፣ የግምገማ ቡድን ይመደብለታል። ይህ ቡድን፤ የቤተሰብ እንክብካቤ አስተናባሪ በሆነ ሰው የተዋቀረ ሲሆን፤ ቤተሰቡን በሂደቱ ጊዜ በሙሉ የሚረዳ እና የግምገማ አስተናባሪው ደግሞ ግምገማውን የሚያዘጋጅ እና IEPን በማዳበር ያዘጋጃል። ከሌሎች ባለሙያዎች ጋር አንድ ላይ በመሆን ይህ ቡድን ወላጆችን ለልጆቻቸው ስለሚያስፈልጓቸው ጉዳዮች የተሻለ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ለማድረግ በማስቻል ግምገማውን ያጠናቅቃል። ከወላጆች ጋር አንድ ላይ በመሆን፣ ቡድኑ ልጁ ለልዩ ትምህርት እና ለተዛማጅ አግልግሎቶች ብቁ መሆኑን በመገምገም ይወስናል። ይህም ከሆነ፣ ቡድኑ IEPውን ይነድፋል።


## የአገልግሎት አቅርቦት (Service Delivery)

ሁሉም የIEP አገልግሎቶች፣ በDCPS ትምህርት ቤቶች ውስጥ፣ በDCPS ሠራተኞች ይሰጣሉ። በDCPS ትምህርት ቤት ውስጥ እስካሁን ያልተመዘገቡ ብቁ የሆኑ ልጆች፣ በየክልል አጎራባች ትምህርት ቤቶቻቸው ወይም በሎተሪ እጣ አማካይነት ቦታ እንዲሰጣቸው ይደረጋል። የክልል አጎራባች ትምህርት ቤት የማይገኝ ወይም ለልጁ የሚያስፈልገውን ፕሮግራም የማያሟላ ከሆነ፣ እነዚህን የሚያስፈልጉትን ፕሮግራሞች አሟልቶ በሚገኝ ቅርብ ትምህርት ቤት ቦታ እንዲሰጠው/ጣት ይደረጋል። የማኅበረሰብ መሠረት ባለው በትምህርት መሠረት መጣያ ፕሮግራም (Head Start program) በሚያካሂድ ትምህርት ቤት፣ የእነሱን IEP በዚያ እንዲሰጥ ይደረጋል። ልጆቻቸው በግል ወይም በሃይማኖታዊ ትምህርት ቤቶች፣ ከIEP ፈንታ በግላዊ የአገልግሎቶች እቅድ (Individualized Services Plan (ISP) አማካኝነት ተመጣጣኝ አገልግሎቶች እንዲሰጣቸው ይደረጋል።



# በብቁነት ሂደቱ-ወቅት ልጠብቀው የሚገባው ነገር ምንድነው?

ልጅዎ አንዳች የሆነ እክል ይኖርበት ይሆናል ተብሎ የሚገመት ከሆነ እና የልጅዎ የIEP ቡድን ግምገማ ያስፈልገዋል ብሎ ከወሰነ፣ ቡድኑ የብቁነት ሂደቱን ያከናውናል። ከ'July 1st, 2018' ጀምሮ፤ ልጅዎን የመገምገም የፈቃድ ስምምነት ከእርስዎ ባገኘ በ60 ቀናት ውስጥ፣ DCPS የብቁነት ሂደቱን ያጠናቅቃል። ይህ ክፍል፤ ጠቃሚ የሆነ የሂደቱን ክፍል የሚያብራራ፣ በቡድኑ ውስጥ በቂ መረጃ ያለው አባል ሆኖ ለመገኘት የሚጠቀሙበትን መረጃዎች ማግኛ፣ እና ለልጅዎ እርዳታዎችን የሚያገኙበት ቦታ ነው።




### በብቁነት መወሰኛ ሪፖርቱ ላይ መመልከት ያለብኝ ምንድነው?

የብቁነት መወሰኛ ሪፖርቱን በሚቃኙበት ጊዜ፣ የሠነዱን መደምደሚያ በማንበብ ይጀምሩ። የሠነዱ ማጠቃለያ፣ በስብሰባው ላይ ሰለሚደረገው ውይይት አጠቃላይ ግንዛቤ እንዲያገኙም ሊረዳዎ ይችላል። ሪፖርቱ፣ የግምገማ መረጃዎችን እና ልጅዎን ለመርዳት የሚገኙ የመገኛ ምንጮችን (resources) ያካትታል።

### ለልዩ ትምህርት (special education) አገልግሎቶች ብቁነት የሚወሰነው እንዴት ነው?

እርስዎን እንደ ወላጅ/አሳዳጊ አድርጎ የሚያካክተው የIEP ቡድን፣ ለልዩ ትምህርት (special education) አገልግሎቶች፣ ልጅዎ ብቁ ሆኖ መገኘቱን ይወስናል። ቡድኑ፤ የወቅቱን የሥራ ናሙናዎችን፣ ለወቅቱ/ላልፉት ጣልቃ ገብ ሁኔታዎች ተማሪዎች የሚያደርጓቸውን እንቅስቃሴዎች፣ የአስተማሪ እና የወላጅ ምላሾች፣ የግምገማ ዘገባዎች (መደበኛ እና ኢመደበኛ የግምገማ መስፈርቶችን የሚያካትት)፣ የተማሪውን መረጃዎች የማጣራት ምርመራን፣ እና በትምህርታዊ መስኮች የተማሪውን በአሁን ጊዜ የአከናወነውን የአፈጻጸም እንቅስቃሴን፤ በዚህ ብቻ ሳይወሰን፤ የተለያዩ በርካታ የመገኛ ምንጮችን (resources) ጨምሮ በማካተት ይመረምራል።

በብቁነት ስብሰባው ላይ፣ እነዚህ መረጃዎች በሙሉ ከተሰበሰቡ እና ምልከታ ከተደረገባቸው በኋላ፣ ቡድኑ፣ ተማሪው ልዩ ትምህርት (special education) አገልግሎቶችን ለማግኘት ብቁ የሚያደርጉትን መስፈርቶች የሚያሟላ እንደሆነ መማጽናት፤ የብቁነት መወሰኛ የመስሪያ-ወረቀት (Eligibility Determination Worksheet)ን ይጠቀማል።

### ምን ዓይነት ግምገማዎች ጥቅም ላይ ውሏል፣ እና ለምን? የውጤት ነጥቦቹን እንዴት ነው ልተረጉማቸው የምችለው?

ግምገማዎች መደበኛ እና ኢመደበኛ ሊሆኑ ይችላሉ። እያንዳንዱ ግምገማ፣ ወደ ሌላ አካል መምራት (referral) ሂደቱ ላይ አስጊ ናቸው ተብለው የተጠቀሱትን መለየት፣ እንዲሁም የተማሪዎን በእያንዳንዱ መስክ ያለውን አጠቃላይ ችሎታንም ጨምሮ ይመለከታል። የግምገማ ውጤቶቹ የሚተረጎሙት፤ በአገልግሎት ሰጪው እና/ወይም በአስተማሪው፤ በግምገማው የመመሪያ-ትዕዛዛቱ ላይ መሠረት ባደረገ ሁኔታ ነው።

እያንዳንዱ መደበኛ ግምገማ የተማሪዎን የትምህርት ውጤት የሚወስን የግምገማ ነጥቦች ጥራት መመዘኛ መስፈርቶችን (rubric) ያካትታል። በሪፖርቶቹ ውስጥ፣ ልጅዎ በእያንዳንዱ ግምገማ እንዴት እንደነበረ ግልጽ በሆነ ሁኔታ የሚጠቅስ እና ይህንን መረጃ ገምጋሚው ያጋራል። እነዚህም፣ በርካታ የደረጃ-መለኪያዎችን፣ ወይም ስኬልድ ስኮርስ (scaled scores)፣ ወይም የተማሪው የክንውን ውጤቶቹን መግለጫን ሊያካትት ይችላል። የእነዚህን ውጤቶች ስፋት እና ከክፍል እኩዮቻቸው ጋር እንዴት ውጤቶቹ እንደተነፃፀሩ ገምጋሚው፣ ለቡድኑ ያሳውቃል። እነዚህ የውጤት ነጥቦች፣ ተማሪ ልጅዎ በክፍል ውስጥ ባሳየውን የክንውን ውጤቶች ላይ በእንዴት ዓይነት ሁኔታ እንደተገናኘ መረዳትዎን እርግጠኛ ካልሆኑ፣ የበለጠ መረጃ ለማግኘት እባክዎን፣ ገምጋሚውን፣ እንዲሁም የአጠቃላይ ትምህርት አስተማሪውን እና የልዩ ትምህርት (special education) አስተማሪውንም ጨምረው ይጠይቁ።

### ምልከታዎች ተደርገው ነበር? ውጤቶቹ ምን ነበሩ?

የክፍል ውስጥ ምልከታዎች (Classroom observations)፣ እንደ ብቁነት ሂደት አንዱ አካል ሆነው ሊካሄዱ ይችላሉ። በምልከታዎቹ ወቅት፣ ምን ዓይነት ስልቶች እንዳሉ፣ የእንክብካቤ መስጫዎች፣ እና እስካሁን በክፍል ውስጥ ሲሰጡ የነበሩትን እርዳታዎችን፣ የተማሪውን በክፍል ውስጥ ያለውን ምላሽ፣ ማንኛውም ተማሪው ሊኖረው የሚችለውን ችግሮች፣ እና የሚያሳያቸውን ማንኛውንም ዓይነት ጥንካሬዎችን፤ ምልከታውን የሚያካሂደው ግለሰብ ይመለከታል። የግምገማው ውጤቶች፣ በአሁኑ ወቅት ያለው የመረጃ ስብስብ ትንታኔ ክፍል (Analyzing Existing Data section) ወይም በግል ግምገማ ሪፖርቶቹ (individual evaluation reports) ውስጥ ሊካተት ይችላል።

### የብቁነት መወሰኛ ሰነዶችን ማግኘት ያለብኝ መቼ ነው?

ማናቸውንም የልጅዎን ግምገማ ውጤት፣ ከብቁነት መወሰኛ ስብሰባ በፊት ቢያንስ 10 ቀን በፊት ማግኘት አለብዎት። ይህ የልጅዎን ለልዩ ትምህርት (special education) አገልግሎቶች ብቁ ሆኖ ለመገኘት የመቻል ሁኔታውን (potential) በተመለከተ፤ ትርጉም በሚሰጥ ሁኔታ በውይይቱ ለመሳተፍ ያስችልዎታል።

### ልጁ ለልዩ ትምህርት (special education) አገልግሎቶቹ ብቁ ሆኖ ካልተገኘ ምን ይሆናል?

በብቁነት መወሰኛ ስብሰባ ላይ ልጅዎ ለልዩ ትምህርት (special education) አገልግሎቶች ብቁ መሆን አለመሆኑን ቡድኑ ይወስናል። በስብሰባው ጊዜ፣ በIEP ቡድኑ ውስጥ ያሉ ግለሰቦች፣ ለመምራቱን (referral) ምክንያት የሆነውን ሌሎች ሥልቶች እና ድጋፎች ይሰጣሉ። ልጅዎ፣ ለልዩ ትምህርት (special education) አገልግሎቶች ብቁ ሆኖ የማይገኝ ከሆነ፣ ልጅዎን ሊረዳ የሚችሉ ሌሎች አማራጮችን፣ ትምህርት ቤቱ መረጃ ሊሰጥ ይችላል። ይህም ልጅዎ የሚያስፈልጉትን ነገሮች እያገኘ መሆኑን እርግጠኛ ለማድረግ፤ የተለያየ-ደረጃ ያላቸውን እርዳታዎችን፣ የማኅበረሰብ አገልግሎቶችን፣ የማስጠናት (tutoring) አገልግሎቶችን፣ የ504 ዕቅድን፣ ወይም ሌሎች እርዳታዎች፤ የመቀጠላቸው ሁኔታ ማለት ሊሆን ይችላል።



# በIEP ውስጥ፤ ምንን መመልከት ያስፈልጋል?

ይህ ክፍል፣ ስለ የግል የትምህርት ፕሮግራም (Individualized Education Program (IEP)፤ የበለጠ ግንዛቤ እንዲኖር ይረዳል። የIEP ቁልፍ የሆኑ ክፍሎች የሚከተሉት ናቸው:

- የተማሪ መረጃ
- በአሁኑ ጊዜ ያሉ የክንውን ደረጃዎች እና ዓመታዊ ግቦች
- የልዩ ትምህርት (Special Education) እና ተዛማጅ አገልግሎቶች
- የክፍል እንክብካቤዎች እና ስቴት-አቀፍ (STATEWIDE) ወይም አማራጭ የግምገማ ተሳትፎ
- የሽግግር ዕቅድ (Transition plan)

## የተማሪ መረጃ

በልጅዎ IEP ላይ ምልከታ በሚያደርጉ ጊዜ፣ የልጅዎ የግል-መረጃዎቹ፤ እንደ (አድራሻ፣ የስልክ ቁጥር፣ የትውልድ ቀን፣ ወዘተ...) ያሉት መረጃዎች በሙሉ ትክክል መሆናቸውን እና በቅርብ ጊዜ የተስተካከለ (up to date) መሆኑን ማረጋገጥ በጣም ጠቃሚ ነው። ይህ መረጃ ትክክል ካልሆነ፤ እባካችሁን፣ የተማሪዎን የጉዳይ-አስፈፃሚን በማነጋገር፣ የትምህርት ቤታቸው መዝገቦች እንዲስተካከሉ (update እንዲደረግ) አሳውቁ።

## ዓመታዊ ግቦች እና በአሁኑ-ጊዜ የሚገኘው የክንውን ደረጃዎች:

ለልጅዎ ዓመታዊ ግቦችን በሚዘጋጁለት ጊዜ፣ የIEP ቡድኑ የሚከተሉትን ያደርጋል:

- በአሁኑ ጊዜ ያለውን የክንውን ለመርዳት፣ የመነሻ የመረጃ ስብስብን (baseline data) ይጠቀማል።
  - የመነሻ የመረጃ ስብስብን (baseline data)፣ በተወሰኑ የቀለም-ትምህርት (academic) ችሎታዎች ወይም ደረጃዎች ላይ፤ ልጅዎ በአሁኑ-ጊዜ እንዴት እየሰራ እንደሆነ፣ መለኪያ-መንገድ ነው።
  - የመነሻ የመረጃ ስብስብን (baseline data) ከተለያየ ቦታዎች: ከመደበኛ ፍተሻዎች (standardized tests)፣ ከምልከታዎች፣ የክፍል ውስጥን መሠረት ያደረገ ግምገማዎች፣ የተማሪ ስራ ናሙናዎች ወይም ከግዛት አቀፍ የምርመራ ውጤቶች፤ ሊመጣ ይችላል።

- IEPው፤ በልጅዎ የሂሳብ፣ የጽሁፍ አገላለጽ (Written expression)፣ እና ንባብ ላይ ባሉ አካባቢዎች ዙሪያ፤ ተያያዥ በሆኑ አገልግሎቶች እና/ወይም በስራ-ላይ ሊውል በሚችሉ ግቦች ላይ፤ መለካት-የሚችሉ ግቦችን እንደያዘ ማረጋገጥ። የIEP ግቦቹ፤ መነሻ የመረጃ ስብስብን (baseline data)ን ተጠቅመው ተቀርጸዋል።

## እያንዳንዱ ግብ፣ በልጅዎ IEP ላይ የሚከተለውን ያደርጋል:

- በግቡ-አካባቢ ላይ፣ አሁን-ያለውን የልጅዎን የክንውን ደረጃ ይዘረዝራል፣
- በIEPው የአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ የሚጠበቀውን የስኬት ደረጃን ይዘረዝራል፤ እንዲሁም
- የተማሪዎቻዎ፣ የእድገት-ሂደት እንዴት እንደተለካ እና የመረጃ ስብስብ (data) በየምን ያህል ጊዜው እንደሚሰበሰብ መግለጽ። በIEP ግቦች ላይ የሚደረጉ የእድገት-ሂደቶች፤ በመደበኛ ወይም ኢ-መደበኛ ሁኔታ ሊለካ ይችላል:
  - ኢ-መደበኛ የሆነ የእድገት መለኪያዎች የሚያካትቱት፤ የተማሪ የሥራ ናሙናዎች (work samples)፣ ኩዊዞች (quizzes) እና ፈተናዎች፣ የባህሪያዊ የእድገት መለኪያ መቆጣጠሪያን ነው።
  - በመደበኛ የሆነ የእድገት መለኪያዎች ሊያካትት የሚችለው፤ መደበኛነት ያለው የውጤት ፈተናዎች (standardized achievement tests)፣ የመጠን መመዘናዎች (rating scales)፣ የጣልቃ-ገብነት (intervention) መቆጣጠሪያ መዝገቦችን፣ እና የስቴት ፈተና ውጤቶችን ነው።





## የልዩ ትምህርት (Special Education) እና ተዛማጅ አገልግሎቶች

በልጅዎ IEP ውስጥ፣ እየተሰጡት ያሉ ልዩ ትምህርቶችን (special education) እና ተዛማጅ አገልግሎቶችን እና እያንዳንዱም አገልግሎት በምን ዓይነት ቦታ እንደሚሰጠው እና አገልግሎቱም በየስንት ጊዜው፣ ልጅዎ እንደሚሰጠው የሚገልጽ የተመደበ ክፍል ይገኛል። ይህ የIEP ቡድኑን፣ ልጅዎን በትምህርት ቤት ሙሉ በሙሉ በመደገፍ ምን ዓይነት አገልግሎቶች እንደሚያስፈልጉት እንዲያውቅ ይረዳዋል።

## የክፍል እንክብካቤ እና ስቴት አቀፍ (STATEWIDE) ወይም አማራጭ የግምገማ ተሳትፎ

ይህ ክፍል፣ ልጅዎ በክፍል ውስጥ ለመርዳት የሚያስፈልጉትን እንክብካቤዎች እና/ወይም ማስተካከያዎችን ይጠቁማል። የሚሰጡት ዓይነት እንክብካቤዎች እና ማስተካከያዎች የሚከተሉትን ሊያካትት ይችላል:

- ተመራጭ የሆነ የመቀመጫ ቦታ (Preferential seating)፣
- የተራዘመ ጊዜ (Extended time)፣
- ተደጋግመው የሚሰጡ እረፍቶች (Frequent breaks)፣
- ማብራሪያ ወይም ትዕዛዛትን ደጋግሞ መስጠት (Clarification or repetition of directions)፣
- ጎልቶ የታተመ ጽሁፍ (Enlarged print material)፣ እና
- ድምጽን ከፍ አድርጎ ማንበብ (Read aloud)

## የሽግግር ዕቅድ (Transition Plan):

የሽግግር እቅዶች እድሜአቸው ከ14 ዓመት እና ከዚህ በላይ ለሆናቸው ተማሪዎች ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በኋላ ለሚገጥማቸው ሕይወት እንዲዘጋጁ ለማድረግ ነው። የሽግግሩም እቅድ የሚከተሉትን ያካትታል:

- ከእድሜ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ የግምገም መረጃ፣
- የልጅዎ የአካዳሚክ፣ የተግባራዊ፣ እና ሥራ የመያዝ ዝንባሌዎቹ፣
- የልጅዎ ጥንካሬ እና የሚያስፈልጉት ነገሮች፣
- ዓመታዊ የሽግግር ግቦች የሚያንጸባርቀው፤ በትምህርት ዓመቱ ወቅት፣ ልጅዎ ምን-ምን ላይ እንደሚሰራ፣ እና
- የረጅም ጊዜ የሽግግር ግቦች ደግሞ፤ ልጅዎ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን አጠናቆ ከተመረቀ በኋላ ምን ማድረግ እንደሚፈልግ፤ የሚያካትት ነው።


# ስለልጅዎ IEP፣ ሊኖሩ የሚችሉ ጥያቄዎች

### በIEP ስብሰባዎች መካከል፣ የቤተሰብ ተሳትፎ ምን ይመስላል?

በትምህርት ዓመቱ ወቅት ሙሉ፣ ቤተሰቦች ከልጃቸው አስተማሪዎች ጋር ግንኙነት እንዲያደርጉ፤ በኢሜል፣ ስልክ፣ ወይም በወላጅ-አስተማሪ ኮንፈራንሶች አማካኝነት፤ ስለተማሪያቸው የቀለም-ትምህርት እድገቶች ፍተሻ-አድርገው እንዲያውቁ ይጋበዛሉ። ከልጅዎ የሪፖርት ካርድ ጋር፣ በየሩብ የዓመቱ-አጋማሽ፤ ወላጆች፣ የIEP እድገት ሪፖርትን ሊያገኙም ይችላሉ። የልጅዎ የIEP አገልግሎቶች፣ የቀለም-ትምህርት እድገት፣ ወይም ግቦች በተመለከተ ጥያቄዎች ወይም ስጋቶች ካሏችሁ፤ ወደ በትምህርት ቤት-ውስጥ መሠረት ያደረገው የIEP የቡድን አባል ሊያቀርቡ ይገባል። ስለ IEPው እና ተያያዥ የሆኑ አገልግሎቶች ለመወያየት፤ ወላጆች የቡድን ስብሰባ የጊዜ-ሰሌዳን የመያዝ መብትም አላቸው።

### እንዴት ነው ልጄን፣ በIEP ግቦቻቸው ላይ ከክፍለጊዜያቸው ውጪ ልረዳው የምችለው?

ልጅዎን፤ በIEP ግቦቻቸው ላይ፣ በመኖሪያ ቤት ውስጥ ለመደገፍ የሚያስችል በርካታ-መንገዶች አሉ። ከመማሪያ ክፍል ውጪ በሆነ-አቀማመጥ፣ ስለ ተወሰኑ እንቅስቃሴዎች፣ ሥልቶችን፣ ወይም የተማሪውን የቀለም-ትምህርት የእድገት ሂደት ለማገዝ-ስለሚያደርጉት ድጋፎችን በሚመለከት፤ የልጃቸውን አስተማሪ እና/ወይም ተዛማች አገልግሎት-ሰጪዎችን፤ ወላጆች አግኝተው ማነጋገር ይችላሉ። ልጅዎን የሚረዱበት ሌሎች መንገዶች የሚከተሉትን ያካትታሉ:




### የልጄ አስተማሪዎች እና ተዛማጅ አገልግሎት ሰጪዎች፣ እንዴት ነው በአንድነት የሚሰሩት?

አስተማሪዎች እና ተዛማጅ አገልግሎት የሚሰጡ፣ ልጅዎን ለመርዳት አብረው በመስራት፤ በመማሪያ ክፍል ውስጥ፣ ለልጅዎ በሚያስፈልጉ ስልቶች እና እርዳታዎች ላይ በተደጋጋሚ ስብሰባ በማድረግ ለመወያየት፤ እንዲሁም እንዲሁም ስለ ልጅዎ እድገት፣ እንዲመቻቹለት ስለተደረጉ ሁኔታዎች፣ እና በየ-IEP ስብሰባዎቹ መካከል የተደረጉ ማስተካከያዎችን የሚያጋሩ ይሆናል። የልዩ ትምህርት መምህራን፣ የአጠቃላይ ትምህርት መምህራን፣ እና ተዛማጅ አገልግሎት ሰጪዎች፣ ልጅዎ እንደሚያስፈልጋቸው ነገሮች የሚያግዙ ነገሮችን፣ በጣም አነስተኛ የሆነ ገደብ ባለበት አካባቢ ማግኘታቸው ለማረጋገጥ በጋራ አብረው ይሠራሉ።

### ስለልጄ እድገት የሚያሳስቡኝ ነገሮች ካሉኝ ምንድነው ማድረግ ያለብኝ?

በIEP ግቦቻቸው አኳያ፣ እድገት እያመጣ ሳይሆን ወይም የኋሊት ቁልቁል እየተጓዘ መሆኑን መስማት አሳሳቢ ሊሆን ይችላል። የሚካሄድው ይህ ከሆነ፣ ስለ አማራጮች ለመወያየት የልጅዎን የልዩ ትምህርት (special education) አስተማሪን ማነጋገር ጠቃሚ ሊሆን ይችላል። ልጅችዎ ስኬታማ ለመሆን የሚያስፈልገውን እርዳታ እያገኘ መሆኑን ለማረጋገጥ፤ የIEP ቡድኑ፣ የልጅዎን አገልግሎቶች፣ እርዳታዎች፣ እንክብካቤዎች፣ እና ማስተካከያዎችን እንደገና ለመገምገም በአንድ-ላይ እንዲሰበሰቡ መጠየቅ ይችላሉ።

### አገልግሎቶች ወቅቱን መጠበቅ ወይም መለወጥ የሚያስፈልጋቸው መሆናቸውን የሚጠቁሙ አመላካቾች ምን ምን ናቸው?

አመልካች የሆኑ ነገሮች የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ:

- እድገትን የሚያመለክት መደበኛ እና ኢ-መደበኛ የግምገማ ውጤቶች፣
- ክህሎቶች/ችሎታዎችን በሚገባ መረዳት፣
- በክፍል ውስጥ አጠቃላይ ክህሎቶችን በሚገባ መጠቀም መቻል፣
- ክህሎቶች ባሉበት በመቆም የመሻሻል እድገት የማይታይበት (Plateau of skills) እና የማያቋርጥ ጣልቃ ገብነት ለተራዘመ-የጊዜው ርዝመት እየተሰጣ ያለበት እና፣
- ውሱን ወይም ምንም የሚታይ እድገት የሌለበት።
- ማናቸውም ለውጦች ወይም አገልግሎቶች ማስተካከያዎች (updates)፣ የIEP ቡድኑ ውሳኔ-የሆነ እና የሁሉንም መረጃ-ስብስብ (data) ምንጮች፣ እንደገና ምልከታ ሊደረግላቸው ያስፈልጋል።

# ልጄ እድገት እያመጣ መሆኑን እንዴት ማወቅ እችላለሁ?

### የልጄ እድገት የሚመዘነው እንዴት ነው?

የተማሪው የእድገት ሂደቶች፣ በበርካታ መንገዶች በአስተማሪዎች እና ተዛማጅ አገልግሎት ሰጪዎች፣ ይለካል። የተማሪ የሥራ ናሙናዎች (work samples)፣ ኩዊዞች (quizzes)፣ ፈተናዎች፣ እና መደበኛ እና ኢ-መደበኛ ግምገማዎች፣ እንዴት የተማሪዎች የእድገት-ሂደታቸውን እንደሚለካ፣ የሚሰጡ ምሳሌዎች ናቸው። እድሜአቸው 14 እና ከዚህ በላይ ለሆናቸው ተማሪዎች፣ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የሽግግር ውጤት ወይም መሻሻል፣ ተማሪው ራስን ችሎ በነጻ በሚያሳየው መንቀሳቀስ አቅም ይመዘናል።

በእያንዳንዱ የIEP ስብሰባ፣ ልጅዎ ባለፈው ጊዜ ከተካሄደው የIEP ስብሰባ በኋላ ያሳካውን የመሻሻል ስኬት በተመለከተ ውይይት ይደረጋል። በውጤት እድገት እርምጃዎች ላይ በመንተራስ እና ቀደም ባሉት ዓመታት ግቦች መቀዳጀት ላይ፣ እና እንዲሁም በአሁኑ ለልጅዎ በሚያስፈልጉት ፍላጎቶች ላይ በመመርኮዝ የልጅዎ ዓመታዊ ግቦች ወቅቱን የጠበቁ እንዲሆኑ ይደረጋል። እነዚህ ግቦች፣ ለሚቀጥለው ዓመት የትኩረት አቅጣጫን በመስጠት ልጅዎ ፈታኝ የሆኑ የአካዳሚክ ትምህርት እንደሚገጥመው ያረጋግጣሉ።

በአጠቃላይ በትምህርት ዓመቱ ወቅት፣ የሚከተሉት ሊያከናውኑ ይገባል:

- በትምህርት ዓመቱ ወቅት፣ ከልጅዎ እድገት ጋር የተያያዘ የመረጃ ስብስብ (data)ን፣ ከልጅዎ አስተማሪዎች እና ተዛማጅ አገልግሎቶች ከሚሰጡ-ሰዎች መጠየቅ። ችግር ወይም ያልተስተካከለ ነገር እንዳለ ከጠረጠሩ፣ የክፍል ውስጥ ግምገማን ለመመልከትና ተማሪዎ እድገት ሊያመጣበት የሚችልበትን መንገድ ለማብዛት፣ የልጅዎን አስተማሪ መጠየቅ አለብዎት።

- ከልጅዎ የባህሪይ ዕቅድ ሁኔታ-ላይ ምልከታ ከሚያደርግ፣ መሪ-የሆነ ካውንስለር ወይም ማህበራዊ ሠራተኛ ጋር፣ ስብሰባ ለማድረግ መጠየቅ። የዚህ አላማ፣ ለባህሪያቸው የሚሰጠው እርዳታ እየሰራ እንደሆነ ለመመልከት እና፣ ካልሠራ ደግሞ፣ ዕቅዶቹን እና ጣልቃ ገብነቶቹን፣ ማንኛውም ጉዳዮች ወይም አሳሳቢ ነገሮች በሚገጥሙ ጊዜ ለማስተካከል ነው።

- ልጅዎ የተሰጠውን የቤት/የክፍል ስራዎች (assignments) ማጥናቀቁን እና ማስገባቱን ለማረጋገጥ፣ የዕቅድ-ማውጫ (planner) ተጠቅሟል። የዕቅድ-ማውጫው (planner)፣ የቤት/የክፍል ስራዎች (assignments) አልተሰሩ-ከሆነ እና በተውሰኑ የቤት/የክፍል ስራዎች (assignments) ላይ፣ ወይም በስርዓት-ትምህርቱ አካባቢ ዙሪያ የሚታዩ ስጋቶች ካሉ ለይቶ-ለማውጣት፣ በወላጆች እና በመማሪያ ክፍል አስተማሪዎች መካከል ግንኙነትን ለመፍጠር ለማገልገል ጥቅም-ላይ ይውላል።

### በከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች የስራ መስክ ላይ መሰረት ያደረገ የመማር ልምዶች፣ እድገቱ እንዴት ነው የሚለካው?

የሽግግር ፕሮግራም-አሰጣጥ አላማው፣ በእያንዳንዱ የሙያ ሁኔታዎች ላይ፣ በተማሪዎች የባህሪይ ሁኔታዎች፣ ችሎታዎች እና በራስ መተማመን ላይ ሊያስከትል የሚችለውን ተጽዕኖ ለመረዳት ነው። የተማሪዎችን የቅድመ-ፕሮግራም ውጤቶችን - ከፕሮግራሙ በኋላ ውጤቶቻቸው ጋር ለማነፃፀር፣ የተማሪዎች የዳሰሳ-ጥናት የሚደረግላቸው ይሆናል።

### የIEP የእድገት ሪፖርቱ፣ ከልጄ ሪፖርት ካርድ ጋር እንዴት ነው ግንኙነት ያለው?

የIEP የትምህርት እድገት ውጤት ማመልከቻዎች፣ ልጅዎ የIEP ግቦቹን በምን ሁኔታ እያሳካ እንዳለ ለእርስዎ ለመግለጽ የሚቀርቡ ልክ እንደ ተማሪ የትምህርት ሪፖርት ካርዶች በየሩብ ዓመቱ እየተዘጋጁ የሚቀርቡ የጽሑፍ ሰነዶች ናቸው። ነገር ግን እነዚህ ግቦች የተለዩ የሂደት መቆጣጠሪያ ሞዴል የሚኖራቸው ሲሆን፣ ልክ እንደ - ተማሪ የትምህርት የሪፖርት ካርዶች ካሉት-ጋር፣ ከተወሰኑ-መደበኛ-ነገሮች ጋር የተቆራኙ ናቸው።

ለእያንዳንዱ የIEP ግብ፣ የእድገት ሪፖርቱ የሚከተሉት መከናወን አለመከናወናቸውን ያሳያሉ:

- ልጅዎ ግቡን ጠንቅቆ-አውቆታል
- ልጅዎ ግቡ ለመምታት እየተጓዘ ይገኛል፣
- ልጅዎ ወደግቡ ምንም ዓይነት እድገት አላደረገም፣
- ልጅዎ ወደኋላ እየወረደ-በመሂድ ላይ ነው (regressing)፣ ወይም
- ወይም ግቡ እስካሁን እንዲታወቅ ሳይደረግ በመቅረቱ አልተጀመረም።

# ልዩ ትምህርት (special education) አገልግሎቶች የት ይሠጣሉ?

የDCPS ልዩ የትምህርት (special education) አገልግሎት ለማግኘት ብቁ ሆነው ለሚገኙ እድሜያቸው ከሦስት እስከ 22 ዓመት ለሆናቸው እክል ላለባቸው ተማሪዎች ስፋት-ያለው አገልግሎቶችን ይሰጣል። እነዚህ አገልግሎቶች ሊሰጡባቸው በሚችሉበት ውስጥ፣ የተለያየ አቀማመጦች የሚገኙ ሲሆን፣ ተማሪዎችም ከሌሎች አነስተኛ እገዳዎች ባላቸው አካባቢዎች ውስጥ አገልግሎቶችን ያገኛሉ። አብዛኛዎቹ የDCPS ተማሪዎች፣ በአጠቃላዩ (መደበኛ) የትምህርት ክፍል፣ በመረጃ መገኛ ክፍል (Resource Room)፣ ወይም ለልዩ ትምህርት የተዘጋጀ ክፍል (self-contained classroom) ውስጥ መስተናገድ ይችላሉ። የተለየ በትምህርት ቤት እና በቤት እንዲሁም በሆስፒታል የሚሰጡ ትምህርቶች በመደበኛው የትምህርት አሰጣጥ ሁኔታ ባልሆነ እጅግ በጣም ውስኑነት ባለው ክልል የሚካሄዱ፤ የሁኔታዎች መመቻቸት በሚገባ ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች የሚካሄድ ነው።

የIEP ቡድኖቹ፣ ተማሪው የሥርዓተ ትምህርቱ ተጠቃሚ እንዲሆን የሚያስፈልጉትን የአገልግሎት ደረጃዎች ይወስናሉ። በIEP ቡድኑ በተወሰነው መሠረት፤ እክል ያለባቸው ተማሪዎች በተቻለ መጠን አንዳች የሆነ እክል ከሌለባቸው አቻ ተማሪዎቻቸው ጋር፤ በተቻለ-መጠን በርካታ ጊዜን ያሳልፋሉ። በእያንዳንዱ ልጅ IEP ውስጥ፣ የሚሰጠው ማመቻቻዎች ተዘርዝረው የሚገኙ እና አጠቃላዩ የትምህርት ሥርዓተ ትምህርት ተጠቃሚዎች እንዲሆኑ ግልጽ-በሆኑ መንገዶች ቀርቧል።

ከጠቅላላ የትምህርት አሰጣጡ ውጪ፣ ከ20 ሰዓታት በላይ የልዩ ትምህርት አሰጣጥ የሚያገኙ ተማሪዎች፤ አገልግሎታቸውን በልዩ ትምህርት የተዘጋጀ (Self-Contained) ክፍል ውስጥ ወይም ስርዓተ ትምህርቱ ተስተካክሎ-ለቀለም ትምህርት ስኬት እገዛ እንዲያደርግ በተዘጋጀው የተለየ ትምህርት ቤት ውስጥ እንዲያገኙ ይደረጋል። የቀለም-ትምህርት ማስተካከያ ለውጦቹ፣ ለተማሪው በሚሰጠው ትምህርት ወይም ይማራል ተብሎ በሚጠበቀው ላይ ይሆናል።




የተማሪው IEPዎች፣ ከመደበኛ ትምህርቱ ውስጥ፣ ከመደበኛ ትምህርቱ ውጪ፣ ወይም በሁለቱም፤ ከመደበኛ ትምህርቱ ውስጥ እና ውጪ፤ አገልግሎቶችን የሚሰጡ ሊሆኑ ይችሉ ይሆናል።

**በአጠቃላይ የትምህርት አሰጣጥ ውስጥ** የሚባለው፤ የሆነ አንዳች እክል ያለባቸው ተማሪዎች ምንም እክል ከሌለባቸው ተማሪዎች ጋር በአጠቃላዩ መደበኛ የትምህርት ክፍል ልዩ የትምህርት አሰጣጥ እና የተዛማጅ አገልግሎቶችን አቅርቦት የሚያመለክት ነው። ሁሉንም ተማሪዎችንና የሆነ አንዳች እክል ያለባቸውን ተማሪዎችን ጨምሮ እጅግ በተቻለ መጠን በአጠቃላዩ ትምህርት መካሄጃ ክልል ሁሉም ተጠቃሚ መሆን እንደሚችሉ DCPS ያምናል።

# ልዩ ትምህርት (special education) አገልግሎቶች የት ይሠጣሉ?

### ማማከር (Consultation)

- በማማከር ሞዴል፣ የአጠቃላይ ትምህርት አስተማሪዎችን፣ ከተማሪዎች የIEP ግቦች ጋር ተጣጥሞ ስለሚጓዝበት መንገድ ለመቀየስ፣ የልዩ ትምህርት (special education) አስተማሪዎችን ያማክራሉ።
- በትምህርቶች እና በትምህርት አሰጣጥ አገልግሎት የመጠቀም፤ አገልግሎቱን ለመደገፍ፣ በሥልቶች እና በማሻሻል ለውጦችን በሚመለከት፣ ተዛማጅ አገልግሎት ሰጪዎች፤ የአጠቃላይ ትምህርት አስተማሪዎችን ያማክራሉ።
- የአጠቃላይ ትምህርት አስተማሪው፣ ከዚህ በኋላ ትምህርቱን ማስተማር ይጀምራል።

### አብሮ ማስተማር (Co-Teaching)

- ስለ ልዩ ትምህርት አሰጣጥ አገልግሎት ትምህርት አሰጣጥ ተግባር፣ የጋራ ማስተማር፣ የሆነ አንዳች እክል ያለባቸው ተማሪዎችን በአጠቃላዩ ትምህርት አሰጣጥ ይዞታ የተለየ የሆነ የማስተማር አገልግሎቶች ለመስጠት በቅራጥነት የቆመ የአገልግሎት መስጫ አማራጭ ነው።
- የጋራ ማስተማር፣ ሁለት ወይም ከዚህ በላይ የሆኑ በሥልጠና የተመሰከረላቸው እና ከእነዚህ በአንዱ፣ በልዩ ትምህርት አሰጣጥ ሥልጠና የተሰጠውና በክፍል ሁሉንም ሆነ ወይም ጥቂት ተማሪዎችን ለማስተማር የኃላፊነት ተግባር ሲወሰድ የጋራ ማስተማርን አብሮ በተግባር ያካሂዳል።
- ይህ ልምድ ከሁለት የትምህርት ባለሙያዎች ለትምህርት ይዘት የተቀናጀ እና የተዋሃደ የማስተማር አቀራረብ ለተማሪዎች ሁሉ የሚያቀርብ ነው።

ሆኖም አንዳንድ ጊዜ፣ ከመደበኛ የትምህርት አቀማመጡ ውስጥ ከሚሰጠው በበለጠ ሁኔታ፣ ተማሪው እርዳታ የሚያስፈልገው ጊዜ ይኖራል። **ከመደበኛ የትምህርት አሰጣጡ ውጪ** የሚለው የሚያመላክተው፤ እንዳች እክል ላለባቸው አጠቃላይ ተማሪዎች፣ ክፍል ወይም የተውጣጣ አጠቃላይ ምድብ ውስጥ ሙሉ የሆነ ልዩ የትምህርት አሰጣጥ እና አገልግሎቶች የሚሰጥን የሚያመለክት ነው። ከIEPዎቻቸው ውጪ ወደ 20 ሰዓት አካባቢ የልዩ ትምህርት አገልግሎቶችን በመረጃ መገኛ ክፍል (resource room) ውስጥ ያገኛሉ።

### የመረጃ መገኛ ምንጭ (Resource) ክፍል ውስጥ

- የመረጃ መገኛ ክፍሎች (Resource rooms)፤ ከመደበኛ የትምህርት ክፍል ውጪ በተለየ ሁኔታ የተዘጋጁ ሲሆኑ፣ ልዩ ትምህርት (special education) አገልግሎቶች ይሰጥባቸዋል።
- በተማሪው IEP እንደተገለጸው፣ የግለሰቦች ፍላጎቶች ላይ እርዳታዎችን በመረጃ መገኛ ክፍሎቹ ውስጥ (resource rooms) ይካሄዳሉ።
- ይህን ዓይነት አገልግሎት የሚያገኝ ተማሪ፣ አንዳንድ እርዳታዎችን በመረጃ መገኛ ክፍሉ (resource room) ውስጥ እና አንዳንዶቹን ደግሞ በመደበኛ የትምህርት ክፍል ውስጥ ያገኛሉ።

የDCPS ለልዩ ትምህርት የተዘጋጀ (self-contained) ዲስትሪክት አቀፍ ክፍሎች፣ 20 ወይም ከዚህ በላይ በሆኑ ሰዓቶች ልዩ የትምህርት አሰጣጥ IEPአቸውን፣ ከመደበኛ የትምህርት አሰጣጡ ውጪ ለሚያገኙ ተማሪዎች ልዩ እርዳታን ይሰጣል። ለልዩ ትምህርት የተዘጋጀ (self-contained) ክፍላችን፣ ከፍተኛ ደረጃ የሆነ ፍላጎት ላላቸው በጉዳተኝነት ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች የበለጠ እርዳታ ለመስጠት የተቀረጹ ናቸው።

### ለልዩ ትምህርት የተዘጋጀ (Self-Contained) ፕሮግራሞች

- ለልዩ ትምህርት የተዘጋጀ (self-contained) የልዩ ትምህርት ክፍሎች በከፍተኛ ደረጃ የተዋቀረና ድጋፍ የሚሰጥበትን፤ ዝቅተኛ የሆነ የተማሪ ቁጥርን ለሠራተኛ አመጣጥና (ratios) ይሠራል።
- ክፍሎች ሁሉ በተመሰከረላቸው በልዩ ትምህርት አስተማሪዎች እና በባለሙያተኞች የተሞላ ነው።
- የአካዳሚክ ትምህርት አሰጣጡ ከጠንካራ የስቴት የማስተማር መስፈርቶች እና ከDCPS የትምህርት አሰጣጥ የወል መስፈርቶች እና የቅደም ተከተል እርምጃ ጋር የሚጣጣም ነው።
- አንዳንድ ተማሪዎች በአጠቃላዩ ትምህርት ሥርዓት ትምህርት ሲጠቀሙ፣ ሌሎች ደግሞ ለወጥ ባለ ሥርዓት ትምህርት ይገለገላሉ።
- ልዩ ሥልጠና የወሰዱ እና የተመሰከረላቸው ተዛማጅ አገልግሎት ሰጭዎች በIEP መሠረት ለተማሪዎች ፍላጎቶች ድጋፍ ይሰጣሉ።
- ተማሪዎች፤ ወይ ከአንዳንድ ሁኔታዎች ተሟልቶ ከመቅረብ ጋር (accommodations) በመደበኛው የስቴት ግምገማ ሊሳተፉ የሚችሉ ሲሆን፣ ሌሎች ደግሞ በተለዋጭ የስቴት ግምገማዎች ላይ ይሳተፋሉ።

በልዩ ትምህርት የተዘጋጀ (Self-Contained) ፕሮግራሞች ውስጥ ያሉ የከፍተኛ ደረጃ ተማሪዎች፤ ወይ ወደ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዲፕሎማ (በመደበኛ ስርዓት ትምህርት) ወይም የከፍተኛ ደረጃ ውጤታማነት ሰርተፊኬት (የተስተካከለ ስርዓት ትምህርት) ለማግኘት በሚወስድ-አቅጣጫ መስራት ይችላሉ። ተማሪዎች እና የእነሱ IEP ቡድን፤ መደበኛ የሁለተኛ ደረጃ ዲፕሎማ ወይም የከፍተኛ ደረጃ ውጤታማነት ሰርተፊኬትን ለማግኘት - ተገቢ-እንደሆነ፤ መወሰይ አለባቸው። ውሳኔውም ከዓመቱ የIEP ቡድን ስብሰባ ከመካሄዱ በፊት ተማሪው ዘጠነኛ ክፍል ሲገባ ወይም 14 ዓመት ሲሆነው ነው።

## ለልዩ ትምህርት የተዘጋጀ (Self-Contained) ፕሮግራም ዓይነቶች

የመገኛ አድራሻ መረጃ: dcps.specialed@k12.dc.gov

| የፕሮግራም ስም | መግለጫ |
|---|---|
| ባህሪይ እና የትምህርት እርዳታ (Behavior & Education Support (BES) | የ'BES' ፕሮግራም፤ ከስሜታዊነት ጋር እክሎች ላላቸው ተማሪዎች የቴራፒውቲክ (therapeutic) መማሪያ አካባቢን የሚያቀርብ እና፣ ውስብስብ የሆነ የባህሪይ ችግሮች ያሏቸውን ተማሪዎች ለመርዳት ስልጠና የወሰዱ የባህሪይ ቴክኒሺያኖች እና ባለሙያተኞች የተሞላ ነው። |
| ግንኙነት እና የትምህርት እርዳታ (Communication & Education Support (CES) | የ'CES' ፕሮግራም የሚያንጸባርቀው፤ ከኦቲዝም ስፔክትረም (autism spectrum) እክሎች ጋር እንደሆኑ የተለዩ እና የተጠናከረ የትምህርት አሰጣጥ እርዳታዎች ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች፣ የተዘጋጀ የ'Applied Behavioral Analysis (ABA)' የመማሪያ አካባቢ ነው። |
| የቅድመ መማር እርዳታ (Early Learning Support (ELS) | የELS ፕሮግራሙ፤ የቅድመ ጣልቃ ገብነት ለሚያስፈልጋቸው የእድገት ዝግመት ላላቸው ተማሪዎች ወይም ሌላ የጤና እክል ያለባቸውን ተማሪዎችን በሙሉ-ሰዓት (full-time) እርዳታን ይሠጣል። |
| እራስን-የቻለ እና የመማር እርዳታ (Independence & Learning Support (ILS) | የ'ILS' ፕሮግራም፤ የማስተዋል ወይም የአዕምሮ የማገናዘብ ጉዳተኝነት አላቸው ተብለው ተለይተው ለነበሩ ተማሪዎች፤ የተስተካከለ ስርዓተ ትምህርትን የሚሰጥ ነው። |
| የሕክምና እና የትምህርት እርዳታ (Medical & Education Support (MES) | የ 'MES' ፕሮግራም፤ ውስብስብ የህክምና ፍላጎቶች እና የአዕምሮ የማገናዘብ ወይም የማስተዋል መዘግየቶች ለሚታዩባቸው ተማሪዎች ቀጥተኛ-የሆነ ነርስ-አገልግሎት እርዳታን በሚሠጡ ሠራተኞች የተሞላ ነው። |
| የዕይታ (Vision) ፕሮግራሞች | የዕይታ (Vision) ፕሮግራም፤ የዕይታ (Vision) እክሎች ላሏቸው ተማሪዎች ማመቻቻዎችን፣ እርዳታዎችን እና ጉድለት-ከሌላቸው እኩዮቻቸው ጎን ለጎን በመሆን በስኬታማነት ለመማር የሚያስፈልጋቸውን ችሎታዎች የሚሰጣቸው ነው። |
| መስማት የተሳነው ወይም የመስማት ችግር ያለበት (Deaf or Hard of Hearing (DHOH) | የ'DHOH' ፕሮግራም፤ መስማት የተሳናቸው ወይም ለመስማት ችግር ያለባቸው ተማሪዎችን፣ በመደበኛነት እያደጉ-ካሉ እኩዮቻቸው ጎን-ለጎን በመሆን በስኬታማነት ለመማር የሚያስፈልጓቸውን ችሎታዎችን እና እርዳታዎችን የሚሰጣቸው ፕሮግራም ነው። |
| ልዩ የሆነ የመማር እርዳታ (Specific Learning Support (SLS) | የ'SLS' ፕሮግራም፤ በልዩ-ሁኔታ የመማር ችግሮች እንዳላቸው የተለዩ ወይም ባላቸው ሌሎች ጉድለቶች ላይ አጠቃላይ የትምህርት ስርዓተ ትምህርት ማግኘታቸው እንዲጨምር፤ የተጠናከረ የቀለም ትምህርት እርዳታዎችን መስጠት ነው። |

### ተማሪዎችን በመኖሪያ ቤት እና በሆስፒታል የትምህርት አሰጣጥን እና በተራዘመ የትምህርት ዓመት ፕሮግራሞች (Extended School Year Programs) አማካኝነትም DCPS፣ እርዳታ ይሰጣል።

| | |
|---|---|
| የመኖሪያ ቤት እና ሆስፒታል ትዕዛዝ (Home and Hospital Instruction (HHIP) | 'HHIP'፤ በቤት-ውስጥ ወይም በሆስፒታል ውስጥ በመታሰራቸው ምክንያት፣ በትምህርት ቤት ውስጥ በአካል ተገኝቶ (in person) ከመማር የሚከለክላቸው የሕክምና ወይም የባህሪይ ጤና ሁኔታዎች ላሉዋቸው ተማሪዎች፤ አገልግሎት የሚሰጥ ነው። |
| የተራዘመ የትምህርት ዓመት (Extended School Year (ESY) | የ'ESY' ፕሮግራም፤ በበጋው (summer) ወቅት ውስጥ፣ ተማሪዎች ለእድገታቸው አስፈላጊ የሆኑ የቀለም-ትምህርት (academic) ችሎታዎችን በመለማመድ እንዲቆዩ ለመርዳትና፣ ወደ አዲሱ ትምህርት መጀመሪያ፣ በልግ (fall) ላይ ዝግጁ እንዲሆኑ እርዳታ ይሠጣል። |

# የአገልግሎት ቦታዎች (Location of Services (LOS):

የመገኛ አድራሻ መረጃ: dcps.specialed@k12.dc.gov

የDSI የአገልግሎት ቦታዎች (Location of Services (LOS) የዓላማ ሂደት፤ ከአጠቃላይ ትምህርት አቀማመጡ ውጪ ከ20-ሰዓታት ወይም በላይ፣ በIEPው ውስጥ የሚገኙትን ተማሪዎች፣ በDCPS ውስጥ የሚገኙትን የልዩ ትምህርት የመረጃ-ምንጮችን (resources) ማግኘት እንዲችሉ ማድረግ ነው።

**ቤተሰብ ሌላ የተለየ የአገልግሎት ቦታን ከፈለጉስ፣ ምን ማድረግ ይቻላል?**

DCPS፣ ከጉዳተኝነት ጋር የሚገኙ ተማሪዎች (students with disabilities)፣ ለቤታቸው አድራሻ ቅርብ-በሆነው ቦታ፣ የፕሮግራም-አሰጣጡ ማግኘት እንዲችሉ ያቀርባል። የልዩ ትምህርት (special education) አገልግሎቶችን ለማግኘት የተማሪው ቦታ፤ በአጎራባች ትምህርት ቤታችከው ክልል ውስጠና የከፍተኛ ደረጃ አዘዋዋሪ ንድፍ (feeder pattern) ውስጥ ይሠጣል። ስለ የአገልግሎት ሂደቱ ቦታዎች፣ አጠቃላይ ጥያቄዎች ካሏችሁ፣ እባካችሁን በdcps.specialed@k12.dc.gov ኢሜል አድርጉ።

**ተማሪው መጓጓዣ (transportation) ከጠየቀስ፣ ምን ይደረጋል?**

መጓጓዣ ተዛማጅ አገልግሎት ነው። ተማሪው ነጻ እና ተገቢ የሆነ የሕዝብ ትምህርት (free and appropriate public education (FAPE) ተጠቃሚ ለመሆን የመጓጓዣ አገልግሎት እንደሚያስፈልገው ከተወሰነ፣ የአሁኑ የትምህርት ቤት የLEA ተወካይ፣ በስቴቱ የትምህርት የበላይ ተቆጣጣሪ ቢሮ (Office of the State Superintendent of Education (OSSE) በሚቆጣጠረው የመጓጓዣ ሥልት ጥያቄውን እንዲያካትት ያደርገዋል።

**ተማሪው በ'My School DC' ሎተሪ አማካኝነት ቦታ ያገኘስ ቢሆን?**

የልዩ ትምህርት ዋና ክፍል፤ በሎተሪ እጣ ሂደት አማካይነት በተመረጠው ትምህርት ቤት ተማሪው ተመዝግቦ ትምህርቱን እንዲቀጥል ለማድረግ የሚያስፈልገውን ጥረት ሁሉ ያደርጋል። ተማሪዎ ሊያስፈልገው የሚችለውን የሙሉ-ሰዓት (full-time) ፕሮግራም፣ እያንዳንዱ ትምህርት ቤት ላይሰጥ እንደሚችል ማስታወስ - በጣም አስፈላጊ ነው። የሎተሪ ውጤቱ፤ በተመረጠው ትምህርት ቤት ውስጥ፣ ለልዩ ትምህርት በተዘጋጀ (Self-Contained) የልዩ ትምህርት (special education) ፕሮግራም፣ ለተማሪው ቦታ ለማግኘቱ  ዋስትና ይሰጠዋል።

**ቤተሰቦች በመጪው የትምህርት ዓመት ስለሚኖረው የቦታዎች አገልግሎት፣ መቼ ይሰማሉ?**

ቤተሰቦች፣ ስለ የሚቀጥለው የትምህርት ዓመት 'LOS'፤ ተማሪው ትምህርት ቤቶችን ከቀየረ፤ በኤፕሪል (April) የጊዜ-አቀማመጥ ውስጥ ይሰማሉ።

**ቤተሰቦች የታሰበውን ትምህርት ቤት መጎብኘት ይችላሉ?**

አዎን! ሁሉም ቤተሰቦች አዲሱን ትምህርት ቤታቸውን እንዲጎበኙ እና በአሁኑ ትምህርት ቤት እና በአዲሱ ትምህርት ቤት መካከል በሚካሄደው የሽግግር ስብሰባዎች ላይም እንዲካፈሉ እናበረታታለን።

**ስለልጁ አዲስ ትምህርት ቤት ቤተሰቦች ጥያቄዎች ቢኖራቸው ማንን ማነጋገር ይኖርባቸዋል?**

የአገልግሎት ቦታዎች (Location of Services) ደብዳቤው፤ የአዲሱን ትምህርት ቤት የመገኛ-አድራሻ እና ለጥያቄዎቻችሁ መልስ የሚሰጠውን በቀጥታ-የምታነጋግሩት የሠራተኛ አባልን መረጃ የያዘ ነው። ቤተሰቦች፤ አዲሱን ትምህርት ቤት ከሚኖሯቸው ማንኛውም ጥያቄዎች ጋር ወይም ጉብኝት-ለማድረግ የጊዜ-ሰሌዳን ለመያዝ፤ ለማነጋገር ምንጊዜም ነፃ ናቸው።

## የሽግግር ፕሮግራሞች (Transition Programs)

የመገኛ አድራሻ መረጃ: dcps.transition@k12.dc.gov

ሽግግር (Transition)፤ ከከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በኋላ፣ ተማሪዎች እና ቤተሰቦቻቸው ለማሰብ የሚጠቀሙበት ሂደት ሲሆን፤ ተመራጭ-የሆነ ውጤቶችን ለመለየት፣ እና ተማሪዎች ግቦቻቸው ላይ ውጤታማ እንዲሆኑ ዕቅወትን እና ችሎታዎችን ማግኘታቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችላቸውን - የትምህርት ቤት እና በማህበረሰብ ላይ መሠረት ያደረገን ልምዶችን ለማቀድ የሚረዳቸው ሂደት ነው።

ተማሪዎች እና የእነሱ IEP ቡድን፣ መደበኛ የከፍተኛ ደረጃ ዲፕሎማ ወይም የከፍተኛ ደረጃ ውጤታማነት ሰርተፊኬት (high school achievement certificate (HSAC)፣ ተገቢ እንደሆነና እንዳልሆነ መወሰን አለባቸው። ውሳኔውም ከዓመቱ የIEP ቡድን ስብሰባ ከመካሄዱ በፊት ተማሪው ዘጠነኛ ክፍል ሲገባ ወይም 14 ዓመት ሲሆነው ነው። አንድ ተማሪ መደበኛ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዲፕሎማን ለማግኘት ለመቀጠል ወይም የከፍተኛ ደረጃ ውጤታማነት ሰርተፊኬትን እንዲያጠናቅቅ የማስቻል ውሳኔ፣ ከተማሪው የትምህርት እርምጃ ጋር ተጣጥሞ እንዲጓዝ ለማድረግ ምን ጊዜም ሊለወጥ ይችላል። ተማሪው የ20 ዓመት ዕድሜ ያለው ወይም ከዚያ የሚያንስ ከሆነ፣ እና መደበኛ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዲፕሎማን ለማጠናቀቅ፣ 5 ክሬዲቶች ብቻ የቀሩት ከሆነ፣ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውጤታማነት ሰርተፊኬቶች፣ እንደ-አማራጭ የሚቀርብ አይሆንም። የIEP ቡድን፤ ተማሪዎች፣ የDCPS መደበኛ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ዲፕሎማ ለማግኘት እድል እንዲኖረው የሚቻለውን ጥረት ሁሉ ማድረግ አለበት።

| **የኢንተርንሽፕ (Internship) ፕሮግራሞች** | |
|---|---|
| ተወዳዳሪነት ያለው የሥራ-ቅጥር ዕድሎች (Competitive Employment Opportunities (CEO)<br>**ክፍል:** *11ኛ/ 12ኛ*<br>**ወደ ምርቃት (Graduation) የሚወስድ-መንገድ:** *ዲፕሎማ (Diploma)* | ‘CEO’፣ በጋራ የስራ-መስክ ፍላጎቶቻቸው መሠረት፤ ተማሪዎችን ከመካሪዎች (mentors) ጋር ያጣምራል። ተማሪዎች በተከታታይ የሙያ-ማሳደጊያዎች ውስጥ እየተካፈሉ በሚገኙበት በተመሣሳይ-ጊዜ ውስጥ እንዳሉ፤ በወር ሁለት-ጊዜ - ከጃንዋሪ (January) እስከ ሜይ (May) ባለው ጊዜ ውስጥ፣ ተማሪዎች እና መካሪዎች (mentors)፣ የ"Career-Focused Project”ን ለመቅረጽ ይገናኛሉ። በበጋ (summer) ወቅት ውስጥ፣ እያንዳንዱ ተማሪ፤ በ80-ሰዓት የኢንተርንሽፕ (internship) አገልግሎት ውስጥ፣ በመካሪያቸው (mentor) የቅጥር-ቦታ ውስጥ፣ ያከናውናሉ። |
| አጠቃላይ ፍለጋዎች (General Explorations (GE)<br>የሥራ ኃይል (Workforce) ማነሳት<br><br>**ክፍል:** *11ኛ/12ኛ ወይም C3/C4*<br>**ወደ ምርቃት (Graduation) የሚወስድ-መንገድ:** *HSAC ወይም ዲፕሎማ (diploma)* | ‘GE’፤ በመማሪያ-ክፍል ላይ መሠረት ያደረገ - ለሥራ ዝግጁነት የትምህርት አሰጣጥ ሲሆን - ወደ ኢንተርንሽፕ (internship) ልምዶች በሽግግር የኮርስ-ስራዎች ውስጥ ለተመዘገቡ ተማሪዎች፣ ከተማሪው የIEP የሽግግር ዕቅድ ከሆነ ከሁለተኛ-ደርጃ በኋላ የቅጥር-ግቦች ጋር አብሮ-እንዲሄድ ተደርጎ የሚሰጥ ነው። |
| **የሥራ ኃይል (Workforce) እድገት ፕሮግራሞች** | |
| የፕሮጀክት ፍለጋ (Project SEARCH) የካፒታል አካባቢ ክልል (Capital Area Region)<br><br>**ክፍል:** *C4 እና እስከ ማመልከቻው ጊዜ ድረስ ከፍ ያለ*<br>ወደ ምርቃት (Graduation) የሚወስድ-መንገድ: *HSAC* | የፕሮጀክት ፍለጋ የካፒታል አካባቢ ክልል (Project SEARCH Capital Area Region (PSCAR)፤ የDCPS አዋቂ-ተማሪዎችን በአዕምሮ የማገናዘብ ጉዳተኝነት ውስጥ ያሉትን ከ18 – 21 ዓመት ዕድሜ ውስጥ ያሉትን፤ ወደ ተወዳዳሪነት ያለው፣ በሆስፒታል ኢንደስትሪ ውስጥ የተቀናጀ ቅጥር ሊያስገኝ በሚችል መንገድ ዝግጁ የሚያደርግ፤ የአንድ-ዓመት በስራ-ላይ እያሉ ስልጠና የሚያገኙበት ፕሮግራም ነው። ተማሪዎች፤ በየ-ዕለታዊ በስራ-ላይ በመገኘት የስራ ልምዶችን በሚያገኙበት፣ በአጋር-ሆቴል ቦታዎች ውስጥ በመሳተፍ፣ የቅጥር-ዝግጁነት የትምህርት-አሰጣጥን ያገኛሉ። የተማሪ የማመልከቻ ሂደቱ፣ በክረምት (Winter) ውስጥ ይከፈታል። |

የሥራ-ኃይል እድገት ማዕከል (Workforce Development Center) በRiver Terrace EC

ክፍል: *C4 እና እስከ ማመልከቻው ጊዜ ድረስ ከፍ ያለ ወደ ምርቃት* (Graduation) የሚወስድ-መንገድ: *HSAC*

የስራ-ኃይል ዕድገት ማዕከል (The Workforce Development Center (WDC)፤ የDCPS አዋቂ-ተማሪዎችን በአዕምሮ የመገንዘብ ችሎታ ወይም ሌሎች የዕድገት ጉዳተኝነት ውስጥ ያሉትን ከ18 – 21 ዓመት ዕድሜ ያላቸውን፤ ለስራ-ቅጥር በማንበረሰቡ ውስጥ ዝግጁ-የሚያደርግ፤ የአንድ-ዓመት - ትምህርት-አሰጣጥን እና በስራ-ላይ ሆኖ መማርን በአንድ-ላይ አቀናጅቶ የሚሰጥ ነው። 'WDC'፤ በአትክልት-ተክል (horticulture)፣ ጤና አገልግሎት፣ እና በእንግዳ አቀባበል (hospitality) እና ቱሪዝም ውስጥ፤ ሥልጠና ይሰጣል። የተማሪ የማመልከቻ ሂደቱ፣ በክረምት (Winter) ውስጥ ይከፈታል።

## አጋዥ የሆኑ ቴክኖሎጂ (Assistive Technology)


አድራሻ: DCPS.assistivetech@k12.dc.gov

አጋዥ ቴክኖሎጂ (Assistive Technology (AT)፤ ከጉዳተኝነት ጋር የሚገኙ ተማሪዎች (students with disabilities)፣ ለእነርሱ አስቸጋሪ የሚሆኑባቸው ስራዎች ለማጠናቀቅ የሚረዳ መሣሪያዎች ናቸው። 'AT'፣ ተማሪዎችን - በንባብ፣ በመፃፍ፣ በመናገር፣ በመገንዘብ፣ እና የክፍል-ውስጥ ቁሳቁሶችን ለመጠቀም ይረዳቸዋል። 'AT'፣ ሁልጊዜ ከፍተኛ-ቴክኖሎጂ (high-tech) የሆነ ዲቫይስ አይደለም፤ ነገር ግን- አነስተኛ ቴክኖሎጂ (low-tech)ን እና ምንም-ቴክኖሎጂ (no-tech) የሆነን - እንደ ወረቀት-ላይ መሠረት ያደረገ በምስላዊነት የተቀናበሩ እና ለግንኙነት የሚያገለግሉ መጽሐፍትንም ሊያካትት ይችላል። አጋዥ የሆኑ ቴክኖሎጂ (Assistive Technology)፤ በተለያየ ምድቦች፤ ለግንኙነት (communication)፣ መማር፣ ለማግኘት የሚጠቅም፣ 'At'ን ሊያካትት ይችላል። ምንም-እንኳን ዕይታ (vision) እና መስማት (hearing)፣ የ'AT' ምድብ-ክፍሎች ቢሆኑም፤ እነዚህ በዕይታ እና ኦዲዮሎጂ ቡድኖች (vision and audiology teams) የሚታገዙ ይሆናል።




በእያንዳንዱ ዓመታዊ የIEP ስብሰባዎች ወቅት፤ የልጅዎ ቡድን፣ በ'AT' የአሰራር-ሁኔታ ላይ ሃሳብ በሚቀርብበት ሂደት ወቅት፣ የ'አጋዥ የሆኑ ቴክኖሎጂ (Assistive Technologÿ) መሣሪያዎች' አስፈላጊነትን ይወያያል። ይህ ውይይት፤ የልጅዎን ጥንካሬ-ጎኖች እና የሚያስፈልጉ-ነገሮችን፣ ፈታኝና-አስቸጋሪ የሚሆኑ ስራዎችን፣ በአሁኑ-ጊዜ በስራ ላይ እየዋሉ ያሉትን መሣሪያዎች እና ልጅዎን እየረዱት እንደሆነ እና አስፈላጊ-ሊሆን ስለሚችለው የ'AT' መሣሪያዎች፤ የሚያካትት ይሆናል።

ቡድኑ፤ ልጅዎ ከ'AT' መሣሪያዎቹ ጥቅም-ሊያገኝበት ይችላል ብሎ ከወሰነ፤ ልጅዎን ሊያግዝ የሚችለውን የ'AT' መሣሪያዎችን ወይም የትኛው የ'AT' መሣሪያዎች ለልጅዎ እገዛ ሊያደግ እንደሚችል ለመወሰን እርዳታ ለማድረግ፣ የትምህርት ቤቱ-ቡድን እርዳታ ያደርጋሉ። እርዳታ ካስፈለገ፤ ከ'AT' ቡድኑ የሚሰጥ እርዳታን፣ ትምህርት ቤቱ ሊጠይቅ ይችላል። የ'AT' ቡድኑ፤ በጣም ተገቢ የሆነውን የ'AT' መሣሪያን ለማግኘት፤ በ'AT' ዲቫይስ በተውሶ-ማግኘት፣ የማማከር-አገልግሎቶች፣ ወይም ሁሉን-አቀፍ ግምገማዎችን በመስጠት ላይ፣ ለልጅዎ በሚወሰንበት ሂደት ላይ፣ የትምህርት ቤቱን ቡድኖች ይረዳል።



## ተዛማጅ የሆኑ አገልግሎቶች (Related Services)

ብዙውን ጊዜ፣ የሆነ እክል ያለባቸው ልጆች በክፍል ትምህርቶቻቸው እንዲሳኩላቸው ለመርዳት ተጨማሪ ድጋፎች እና አገልግሎቶች ያስፈልጓቸዋል። ሥርዓተ ትምህርቱን ከልጁ ፍላጎት ጋር የሚጣጣም እንዲሆን ለማድረግ የሆነ አንዳች እክል ያለባቸው አንዳንድ ተማሪዎች የልዩ ትምህርት አሰጣጥ ብቻ ያስፈልጓቸዋል። በሌሎች ጊዜያት፣ በክፍል የሚሰጠውን ትምህርት ለመደገፍ፣ ተማሪዎች የተወሰኑ ተዛማጅ አገልግሎቶች እንዲሰጣቸው ይደረጋል።

**ተዛማጅ የሆኑ አገልግሎቶች ዓይነቶች:**

| ተዛማጅ የሆኑ አገልግሎቶች (Related Services) | መግለጫ |
|---|---|
| **ትምህርታዊ ኦዲዮሎጂ** (Educational Audiology) (speech.audiology@k12.dc.gov) | የተማሪዎች የመስማት ክህሎቶች እና የማጣሪያ ምርመራ፣ የአካዳሚክ፣ የመገናኛ፣ እና/ወይም ማኅበራዊ ክህሎቶች ላይ ጫና የሚያሳድሩ እና በመስማት፣ በማዳመጥ፣ ሂደቶች ላይ የሚያተኩሩ ናቸው። ኦዲዮሎጂስቶች (Audiologists)፣ የተማሪውን የመስማት እና የማዳመጥ ሂደት ችሎታን በመገምገም እና ተገቢ የሆኑ ተግባር ላይ የሚውሉ ቴክኖሎጂዎችን የሚደግፉ አካላት ናቸው። |
| **የአዕምሮ ጤና እና የባህሪ እርዳታ (Mental Health and Behavioral Support)** (school.mentalhealth@k12.dc.gov) | የአእምሮ ጤንነት እና የባህርይ ድጋፍ አገልግሎቶች ቡድን፣ ተማሪዎች በትምህርቶቻቸው ላይ የመሳተፍ እና የተጠቃሚነት ክህሎቶች ላይ ጫና የሚያሳድሩ፣ በትምህርት ቤት፣ በመኖሪያ ቤት እና በማህበረሰቡ ውስጥ ስለ ሚገጥሟቸው ጉዳዮች ከተማሪዎች ጋር አብረው የሚሠሩ የDCPS ማኅበራዊ ጉዳይ ሠራተኞችን ይይዛል። እነዚህ አገልግሎቶች፣ የቡድን ወይም የግል የማማከር ተግባርን፣ የቤት ጉብኝቶችን፣ እና ማኅበራዊ፣ ስሜታዊ፣ እና የባህርይ ግምገማዎችን ያካትታሉ። |
| **ኦኩፔሽናል ቴራፒ** (Occupational Therapy) (dcps.OTPTtherapyprogram@k12.dc.gov) | የኦኩፔሽናል ቴራፒ (Occupational therapy) ባለሞያዎች፣ በትምህርት ቀኑ ሙሉ፣ ልጁ በሚሳተፍባቸው እንቅስቃሴዎች ላይ እርዳታ ይሰጣል። ትምህርት ቤትን መሠረት ያደረገው ባለሙያ፣ በቀለም ትምህርት ስኬቶች እና በማህበራዊ ተሳትፎዎች ውስጥ፣ በትምህርት ቤቱ ውስጥ ባሉ ተደጋግመው የሚደረጉ ነገሮች (routines) ላይ በሙሉ፤ እረፍትን (recess)፣ የክፍል ውስጥን እና የካፌቴሪያ ጊዜን ጨምሮ፤ የአካል እንቅስቃሴን በማበረታታት እርዳታ ይሰጣል። |
| **ፊዚካል ቴራፒ (Physical Therapy)** (dcps.OTPTtherapyprogram@k12.dc.gov) | የፊዚካል ቴራፒ ባለሙያዎች (Physical therapists)፤ ግለሰቦች ንቅናቄዎችን፣ እንቅስቃሴን፣ እና ክንውኖችን እንዲጠብቁ እና እንዲያሻሻሉ፤ ከዚያም ባሻገር አማራጭ የአፈጻጸም ክንውን ለማካሄድ የሚያስችሉ እና ጤንነትን፣ ደህንነትን፣ እና የኑራት ደረጃውን የጠበቀ ህይወት እንዲመሩ የሚረዱ የጤና ባለሞያዎች ናቸው። የፊዚካል ቴራፒ ባለሙያው (Physical therapists)፤ ማካካስን፣ ጉድለቶችን ማቃናት ወይም ማረምን እና የመከላከል ሥልቶችን እና ችግሩን መቀበል እና መለማመድን ጨምሮ በተግባራዊ እንቅስቃሴ ላይ ማተኮር እና ደህንነት ላይ፣ በክንዋኔዎች እንቅስቃሴዎች ላይ ተሳትፎን ጨምሮ የቴራፒ ጣልቃ ገብነትን ያከናውናል። |
| **ሥነ ልቦና (Psychology)** (school.mentalhealth@k12.dc.gov) | የሥነ ልቦና ባለሞያው (psychologist)፣ የሥነ ልቦና እና የእድገት መፈተኛዎችን በመስጠት፣ ስለልጁ ባህሪ እና የመገንዘብ እንቅስቃሴዎቹ የተሰጠን መረጃ በመተንተን፣ እና ከትምህርት ቤት ሠራተኛ እና ወላጆች ጋር በመሆን እነዚህን ውጤቶች ትርጓሜ በመስጠት፤ ተማሪዎችን እና ትምህርት ሰጪዎችን ያግዛሉ። |
| **የንግግር-ቋንቋ ፓቶሎጂ (Speech-Language Pathology)** (speech.audiology@k12.dc.gov) | የንግግር-ቋንቋ ፓቶሎጂ ባለሙያ (speech-language pathologist)፣ ከቃል ቋንቋ እና ግንኙነቶች ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ልዩ የሆነ እክሎችን እና መዘግየቶችን በመለየት እና እርዳታዎችን ለልጆች ይሰጣል። የንግግር-ቋንቋ ፓቶሎጂ ባለሙያው (speech-language pathologist)፣ ተማሪዎች የበለጠ ራሳቸውን እንዲችሉ፣ በአሁኑ ጊዜ ያለውን የጣልቃ ገብነት ቴክኖሎጂ እና ዘዴዎችን ይጠቀማሉ። |

## የተመረጠ 504 ፕሮግራም

የሚገኙበት አድራሻ: 504@k12.dc.gov

ክፍል (Section) 504 ፕሮግራም የተሰየመው ለክፍል 504 መልሶ የማቋቋም (of the Rehabilitation Act) የ1973 ድንጋጌ፣ የፌደራላዊ ህግ፣ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች የሆነ አንዳች እክል ያለባቸው ተማሪዎች በትምህርት ቤቱ አጠቃላይ ሥርዓተ ትምህርት እና በትምህርት እድሎች መጠቀም የሚያስችል ነው።

ከልዩ ትምህርት በተለየ መልኩ፣ ብቁ ሆነው ለሚገኙ ተማሪዎች ልዩ የሆነ ትምህርት እንዲሰጥ ክፍል (Section) 504 አያዝም። በዚህ ፈንታ፣ ለክፍል (Section) 504 ፕሮግራም ብቁ ሆነው ለሚገኙ አንዳች የሆነ እክል ላለባቸው ተማሪዎች፣ በDCPS ትምህርት ቤቶቻቸው ለመማር የሚያስፈልጓቸው የአጠቃላይ ሥርዓተ ትምህርት እና ሌሎችም እድሎች የተመቻቹ ሁኔታዎች እንዲቀርቡላቸው እና/ወይም አገልግሎቶች እንዲመቻቹላቸው ያረጋግጣል።

### ብቁነት (Eligibility)

ከዚህ በታች የተጠቀሱት ሦስቱም በሙሉ በአንድላይ ሲሳኩ፣ አንድ ተማሪ በክፍል (Section) 504 ሥር ብቁ ይሆናል:

- ተማሪው ዋና የሕይወት ተግባር ለማከናወን ከፍተኛ አካላዊም ሆነ  አእምሮአዊ እክል ያለበት ከሆነ፣

የብቁነት መወሰኛ፣ በተማሪዎ ትምህርት ቤት ውስጥ በ504 ቡድን ይከናወናል።

### ለክፍል (Section) 504 ሂደት:

| | |
|---|---|
| መመራት (Referral) | ወላጆች/አሳዳጊዎች ልጃቸው ለክፍል 504 አገልግሎት ብቁ ሊደርገው የሚያስችል አካላዊም ሆነ ወይም አእምሮአዊ እክል አለበት ብለው የሚያምኑ ከሆነ፣ የልጃቸውን እክል ጉዳይ ወደ ሌላ አካል እንዲተላለፍ እንዲያደርጉ ይጋበዛሉ። ወደ ሌላ አካል የማስተላለፉ ተግባር በክፍል (Section) 504 ወደሌላ አካል መምራት ቅጽ (በልጅዎ ትምህርት ቤት በሚገኝ) አማካይነት ለትምህርት ቤቱ በመጻፍ፣ በኢሜይል ወይም በስልክ ወይም በግል በማነጋገር የማስተላፉ ተግባር ሊካሄድ ይችላል። |
| ተጨማሪ መረጃዎች | ወደ ሌላ መመራት (referral) ቅጹ፣ አንድ ጊዜ ለትምህርት ቤቱ ከደረሰ፣ የ504 ቡድኑ ወላጅን/አሳዳጊን ማናቸውንም የህክምና መረጃ ወይም ተጨማሪ መረጃ እንዲያቀርብ እና የ504 የብቁነት ስብሰባ ላይ እንዲገኝ ይጋብዛል። |
| የብቁነት (Eligibility) ስብሰባ | በብቁነት መወሰኛ ስብሰባ ላይ፣ ተማሪው ብቁ ይሆን እንደሆነ ለመወሰን ቡድኑ ያለውን መረጃ ሁሉ እየመረመረ ያጣራል። |
| የ504 ዕቅድ ስብሰባ | ተማሪው ብቁ መሆኑ ከተወሰነ፣ ወላጅን/አሳዳጊን የሚይዘው የ504 ቡድን፣ ተማሪው በትምህርት ቤት በአጠቃላይ ትምህርት ሥርዓተ ትምህርት መገልገል እንዲችል የሚያስፈልጉትን ሁኔታዎች ተሟልተው እንዲገኙ በማመቻቸት፣ ከዚያ ለተማሪው የ504 እቅድ ይነድፋል። |
| ዓመታዊ ምልከታ | የ504 ቡድን፣ የተማሪው የ504 እቅድ ለውጥ ያስፈልገው ወይም አያስፈልገው እንደሆነ ለማጣራት፣ ለማቀድ እና ለመወሰን፤ በየዓመቱ ይሰበሰባል። የ504 ቡድን በተጨማሪ፣ የተማሪው ለክፍል 504 ብቁነትን በየሦስት ዓመቱ ለማጣራት ይመረምራል። |